" ሕዝቤ እውቀት ከማጣቱ የተነሣ ጠፍቶአል። " (ት.ሆሴ 4:6)

በድርሳነ ፅዮን ላይ ስለ ቡና ስለ ጫትና ስለ ጥንባሆ ምን እንደተጻፈ ያንቡ " በእርግጥ መፅሀፏ አሁን ከገበያ ጠፍታለች ለማንበብ በጣም እጓጓላት ነበር እግዚአብሔር በፈቀደ ጊዜ ከማውቀው ሰው እጅ ላይ አገኘኋት ተበድሬ አነበብኳት ካነበብኩትም ጥቂቱን ክፍል ለበረከት እነሆ እግዚአብሔር ከሁላችን ጋር ይሁን።

፩ .ተአምር

ተአምሪሀ ለጽዮን እምነ ሰማያዊት ጸሎታ ወበረከታ የሀሉ ምስለ ሕዝበ ክርስቲያን ለአለም አለም አሜን።

ሕዝበ ክርስቲያን ሆይ ልንገራችሁ ስሙ የተፃፈ መፅሀፍ ሁሉ እኛ ልንመከርበት ተፅፏል እንዳለ ጳውሎስ ሮሜ 13÷4 ከአዳም ልጆች ወገን ሴሩህ የሚባል ሰው ነበር ለሴሩህም ስሙ ብኑ የሚባል ልጅ ተወልዶ በህፃንነቱ ሞተበት በብኑ ስም በተቀረፀው ጣኦት መመለክ ተጀምሯል በመቃብሩም ላይ ሰይጣን የሚወዳት ከሱስ የተነሳ ፆምን የምታሸር የከፋች እፅ በቀለች ይኸውም ከስንዴ መካከል እንክርዳድን የዘራ ጠላት ዲያቢሎስ ካለችበት አምጥቶ ዘራት።ማቴ 13÷28

በብኑ ስም ቡን ተብላለች ቡና ማለት ነው ማክሰኞ ከተፈጠሩት ዕፅዋት መልካምና ክፉ ክፉ ፍሬ ያፈራል እንዳለ።ማቴ7÷12

እስማኤላውያን የሚያመልኳቸው የጣኦታቸው መሥዋዕት ሆነች የተንባላት አለቃ የሚሆን እስከ መሐመድም ትደርሳለች ተንባላትም ያለ እሷ ሌላ አይሰውም ተንባላት ማለት የመሐመድ ተከታዮች ናቸው ጣኦት የሚያመልኩ ባለዛሮችም ይህችኑ ይሰዋሉ የቡና ሱስ ያዘን ብለው ጾምን የሚሽሩ በበአል የሚወቅጡ ራሳችንን አመመን በማለት በውስጣቸው ላደረ ለሱስ ጋኔን ይሚገብሩ ብዙዎች ናቸው ወደ ቅዳሴም እንዳይሄዱ በጠዋት እሷን እየጠጡ ይችም ዕፅ ክፉ ሁና ሰውን ስታሳስት ትኖራለች ።

በሰለሞን ምሳሌያት ትርጓሜ 13÷10 ክፉውን ሰው ወንድሜ እንደዚህ ያለ ነገር ለምን ታደርጋለህ ቢሉት እንደፈለግሁ ልሁን ልሁን ለራስህ እወቅ እያለ ይነቅፋል ይላል እኛስ መንቀፍ ትተን ከቶ ብንተው ምን ይጎዳናል ትርጓሜ ወንጌልም ዮሀንስ የሚያሰክር ቡን አልጠጣም መንፈስ ቅዱስ አድሮበታልና ይላል ሉቃ 1÷15

እኛስ በአርብ ቀን መንፈስ ቅዱስን ተቀብለን የለምን የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ አካላችን የሱስ ጋኔን ማደሪያ ለምን ይሆናል ።

የሰማያዊት የእናታችን የጽዮን ጸሎቷና በረከቷ ከኛ ጋር ይሁን ለዘለአለሙ አሜን ።

፪ . ተአምር

የሰማያዊት የእናታችን የጽዮን ተአምር ይህ ነው ጸሎቷና በረከቷ ከኛ ጋር ይሁን ለዘለአለሙ አሜን።

ሌላም የሚያስረዳና ልቦናን የሚያፀና ስሙ ልንገራችሁ የተንባላት መምህር የሚሆን መሀመድ የሚባል አንድ ሰው ከመካዱ የተነሳ ከአጋንንት ጋር ይውላል ከእለታት በአንዱ ቀን ሲሰግድ በልጅነቱ ያመው የነበረው እራስ ምታት ይነሳበታል

በዚህ በሽታ እየተሰቃየ ሳለ ከእለታት በአንዱ ቀን ዲያቢሎስ በተንኮሉ ያስተው ዘንድ ወደ እሱ መቶ ወዳጄ መሀመድ ሆይ ምን ሆንክ ይለዋል እራስ ምታት ነበረብኝ በዚህ ደዌ እጨነቃለሁ ይለዋል እራስ ምታት በሽታም የሚሆን በት እሱ እራሱ ዲያቢሎስ ነው።

መሀመድም መልሶ ከፍተኛ እራስ ምታት ነበረብኝ በዚህ ደዌ እጨነቃለሁ ይለዋል የእራስ ምታት መድሀኒት ብነግርህ ታደርገዋለህን ይልቦናዬንም ፈቃድ ትፈፅማለህን ይለዋል መሀመድም ካዳነኝ አዎ ያልከኝን ሁሉ አደርገዋለሁ ብሎ ይመልስለታል።

ከዚህ በኋላ ዲያቢሎስ እፀ ጌት የተባለች ጫትን እፀ ኩስራ የተባለች ቡናን እፀ አስጥራጢስ የተባለች ጥንባሆን ካሉበት ቦታ አምጥቶ መድሀኒት ናቸው ብሎ ይሰጥዋል ይህንንም ቡና ከጠጣህ ፈጥነህ ትድናለህ ለልጅ ልጅህ ዘመን በመካ መዲና ሰዋ ብሎ ቆልቶ ያሳየዋል።

መሀመድም ብረት ምጣድ አግሎ ሲቆላ እንደ መልኬ ከሰል አስመስለህ አጥቁረህ ትቆላዋለህ ይለዋል እንዳለው አድርጎ ከሰል አስመስሎ ይቆላል ሁልጊዜም እንደዚሁ ካላከሰልክ መድሀኒት አይሆንልህም ይለዋል እራስ ምታቱም ለጊዜው የተወው ይመስለዋል ኋላ ግን ሰአት እየጠበቀ ይነሳበታል ።

እናታችን ጽዮን ሆይ ረድኤትሽ ይጠብቀን ለዘለአለሙ አይለየን።

፫. ተአምር

የሰማያዊት እናታችን ጽዮን ተአምር ይህ ነው ፀሎቷና በረከቷ ከሁላችን የጥምቀት ልጆች ጋር ይሁን ዛሬም ዘወትርም ለዘለአለሙ ይደረግልን።

መሐመድ እፀ ኩስራ የተባለችውን ቡናን በሚያፈላና በሚሰግድ ጊዜ ፍርቃን የተባለውን መፅሀፍ ከመውደዱ የተነሳ ዲያቢሎስ ወደ እርሱ ይመጣና በምእራፍ 28 ላይ የሚገኘውን ቃላት ፃፈው ነገር ግን እንዳያነቡት እጠረው ወገኖችህ ተንባላት የታጠረውን እንዳያነቡት የታጠረውን አታንቡ ሌላ ያልታጠረውን ግን አንብቡ ብለህ አስተማራቸው ይለዋል።

ተንባላትም ይህን ትእዛዝ ይዘው ይፅፉታል እንዳያነቡት ግን ዙሪያውን ያጥሩታል ይህን ትዕዛዝ ተደፋፍሮ ያነበበውና የተረጎመው ግን የተረገመ ይሁን ሥራ ሥሩ ይበጣጠስ አጥንቱ ይሰበር ሥጋው ይበጠስ ምላሱ ይቆረጥ አይኑ ይታወር ይላሉ።

ዲያቢሎስ ለእርሱ እንዲህ ብለህ አውግዝ ይለዋል ከዚህ በኋላ መሀመድ እንዲህ ብሎ ዘመዶቹን ያወግዛቸዋል የታጠረውም ጽህፈቱ ሻውዚን ነፋህነ ነፋህነ ወረምሃ ላቲ አሕሳነት ኢናበሀ ይላል ይህም ማለት ከሶስቱ አካል አንድ ይወርዳል በድንግል ማርያም ማህፀን ያድራል ከድንግል በድንግልና ይወለዳል ይህም ማለት ወንድ ሳታውቅ በድንግልና ወለደች ከእሷ ተወለደ ማለት ነው።

አላህ ማለታቸው አምላክ ማለታቸው ነው ፍርቃን በተባለው መፅሀፋቸው እንጅሎሙ ይላሉ ይህም ማለት ወንጌላቸው ከሶስቱ አካል አንዱ አካል ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ተወለደ ትላለች የዲያብሎስን ህግና የመሀመድን ውግዘት እንዳያልፉ ያጥራሉ የታጠረውን አንብበው መረዳት አቅቶአቸው አምላክ አይወርድም አይወለድም ይላሉ እንዲህ ብለውም ያስተምራሉ።

ሶስቱ እፅዋት እፀ ጌት ጫት እፀ ኩስራ ቡና እፀ ሰጥራጢስ ጥንባሆ እነዚህ ስማቸው የተለያየ ቢሆንም ግብራቸው አንድ ነው የሱስ አጋንንትን ያሳድራሉና ቡናና ጫት የመሀመድ መስዋእት ናቸው ዲያቢሎስ እንጦርጦስ የወረደበት በመካ መዲና /የሚሰውዋቸው/ የሚያቀርባቸው መስዋእት እነዚህ ናቸው ይህም የተለመደው /የሚደረገው/ በግፃውያን ተንባላት ዘንድ

ነው።

ወደ ኢትዮጵያ እንዴት እንደመጣ እንነግራችኋለን በመሀመድ ስርአትና ህግ የሚጓዙ አቦልና ቶና በረካ የሚባሉ ሶስት ሰዎች ለንግድ የመጡ መስለው ከአምስት መተንብላን ጋር እነዚህን እፅዋት ይዘው ይመጣሉ እነዚህም ሶስት እፅዋት ጫትና ቡና ጥንባሆ አህዛብ ለሰይጣን የሚያቀርቧቸው የጣኦት መስዋእት ናቸው።

ለክርስቲያን ግን እነዚህን መብላት መጠጣት አይገባም እነዚህን የበሉና የጠጡ ካልተጠመቁ ሰዎች ጋር በገሀነም ይፈረድባቸዋል መፅሀፍ የተናገረውን አልሰማችሁምን በአምሳሉ እግዚአብሔር የፈጠረው የመጀመሪያው አዳም አትብላ የተባለውን ክፉ እፀ በለስ በልቶ ከልብሰ ብርሃን እንደተራቆተና ከተድላ ገነት ወጥቶ የፍዳ የመርገም የፍርሀት የስቃይ ቦታ ወደ ምትሆን ወደዚች ምድር ተሰደደ ክፉዎች እፅዋትና መልካሞች እፅዋት እንዳሉ ጌታችን በወንጌል ነግሮናል።እነዚህን እፅዋት በመብላት በመጠጣት አትሳቱ ይህንም አድርጋችሁ ወደ ቤተ እግዚአብሔር ሄዳችሁ አታርክሱ።

ሰማያዊ እናታችን ጽዮን ሆይ አማላጅነትሽና ቃል ኪዳንሽ ይጠብቀን ዛሬም ዘውትርም ለዘለአለሙ ይደረግልን።

ስለዚህ አንዳንድ ገዳማት ይህንን አስተምህሮ በግልጥ ይናገራሉ ለምሳሌ በፃድቃኔ ማርያም ፀበሏን የጠጣ ቡና መጠጣት እንደማይችልና እምነቷንም ሆነ ፀበሏን ቡና የሚፈላበት ቤት ውስጥእንደማይችልና እምነቷንም ሆነ ፀበሏን ቡና የሚፈላበት ቤት ውስጥ ማኖር እንደማይቻል ሰምቻለሁ ሌላው በበሬ ሀገር መድኃኒዓለም ገዳም ቡና የሚጠጡ ከእምነቱ መቅመስ እንደማይችሉ ገዳሙን ከመሰረቱት ታላቅ አባት ሰምቻለሁ እናም እህት ወንድሞቼ ውሳኔው የእናንተነው ነገር ግን አቅረብኩ ለከ ማየ ወእሳት ደይ እዴከ ሀበ ዘፈቀድከ እንዲል የመዳንቀን አሁን ነው በነዚህ ሱሶች የተያዝን ልንወጣይገባል " ሁሉ ተፈቅዶልኛል፥ ሁሉ ግን አይጠቅምም። ሁሉ ተፈቅዶልኛል፥ በእኔ ላይ ግን አንድ ነገር እንኳ አይሠለጥንብኝም።"

(1ቆሮ6:12)

ኣቅረብኩ ለከ እሳተ ወማየ ደይ እዴከ ሃበ ዘፈቀድከ